የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ የካቲት ፯ ቀን
፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.43
ADDIS ABABA, 16th February, 2016

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፬/፪ሺ፰ ዓ.ም

ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባሎች እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች መወሰኛ (ማሻሻያ) አዋጅ……………………………………………ገጽ ፰ሺ፰፻፶፰

**CONTENTS**

Proclamation No.934 /2016

Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges (amendment) Proclamation ………………………………………………page 8858

አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፬/፪ሺ፰

**ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣የምክር ቤት አባሎችና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባሎችና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባሎች እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች መወሰኛ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፬/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**PROCLAMATION No.934 /2016**

**APROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF RIGHTS AND BENEFITS OF OUTGOING HEADS OF STATE AND GOVERNMENT, SENIOR GOVERNMENT OFFICIALS, MEMBERS OF PARLIAMENT AND JUDGES**

**WHEREAS**, it has become necessary to amend the Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges Proclamation number 653/2009 ;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopian Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges (amendment) Proclamation No.934 /2016".

**፪.ማሻሻያ**

ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባሎች እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

፩/ በአዋጁ በየትኛውም ክፍል “ፓርላማ” ተብሎ የተጠቀሰው ቃል “የፌደራል ምክር ቤቶች” በሚል ተተክቷል፡፡

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተተክቷል፦

፯/ “የምክር ቤት አባል” ማለት አፈጉባኤን፤ ምክትል አፈጉባኤን እና ማንኛውም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልን እና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የፌደሬሽን ምክር ቤት በቋሚነት የሚሰራ የፌደሬሽን ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባልን ያጠቃልላል፤”

፫/ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፯) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፰) ተጨምሮ ነባሮቹ ንዑስ አንቀፆች እንደ ቅደም ተከተላቸው (፱)፣ (፲)፣ (፲፩)፣ (፲፪)፣ (፲፫)፣ (፲፬)፣ (፲፭)፣ (፲፮)፣ (፲፯)፣ (፲፰)፣ (፲፱) እና (፳) ሆነው ተሸጋሽገዋል፦

“፰/ ‘የቋሚ ኮሚቴ አባል’ ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ፌዴሬሽን ምክር ቤት በቋሚነት የሚሰራ የቋሚ ኮሚቴ አባል ነው፤”

፬/ ከአዋጁ አንቀፅ ፶፮ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፶፯ ተጨምሮ ነባሮቹ አንቀጾች እንደ ቅደም ተከተላቸው ፶፰፣ ፶፱ እና ፷ ሆነው ተሸጋሽገዋል፦

፰ሺ፰፻፶፰

“**፶፯.ተፈጻሚነት**

**2. Amendment**

The Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges Proclamation No. 653/2009 is hereby amended as follows:

1/ The word “parliament” appearing anywhere in the proclamation is hereby replaced by the word “Federal Houses”

2/ Sub-article (7) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (7):

7/ ‘Member of Parliament’ include the Speaker, the Deputy Speaker and any member of the House of Peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and member of the House of Federation working permanently in the standing committees of the House of Federation;”

3/ The following new sub-article (8) is added after sub-article (7) of Article 2 of the Proclamation and the existing subsequent sub-articles are renumbered as sub-articles (9), (10), (11), (12), (13), (14), (15), (16), (17), (18), (19) and (20) :

8/ ‘Member of Standing Committee’ means member of the House of People’s Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia or member of the House of the Federation working permanently in a standing committee;”

4/ The following new Article 57 is added after Article 56 of the Proclamation and the existing subsequent Articles are renumbered as Article 58, 59 and 60:

ይህ አዋጅ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ፌዴሬሽን ምክር ቤት በቋሚነት ሳገለገሉና ለተሰናበቱ የቋሚ ኮሚቴ አባላት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡"

፫.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

›

**አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

"**57. <u>Application</u>**

This Proclamation shall also apply to those members of the House of the Federation who served the House of Federation as permanent members of the standing committee from the time of entering into force of Proclamation No. 653/2009 and left the House."

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of February 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**
**REPUBLIC OF ETHIOPIA**